በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን



ወደ ጎን

1 “እነሆ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱ ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና" ብሎ ለእረኞች ያበሰረው ማን ነው?(12)

2 “ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ _____ ተብሎ ይጠራል።”(7)

3 ለሰብአ ሰገል ተገልጦ በሌላ ጎዳና እንዲሄዱ እንጂ ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ የነገራቸው መልአክ(8)

4 ጌታችን በቤተልሔም በየት ተወለደ?(9)

5 የስሙ ትርጓሜ “መልእክተኛዬ” የሆነ ነቢይ(5)

6 “እነሆ፥ በኤፍራታ ሰማነው፥ በዱር ውስጥም አገኘነው።” የሚለው ጥቅስ የሚገኝበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል(7)

10 በማቴዎስ ወንጌል 2፡5 ላይ “እንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና” የሚለውን የትንቢት ቃል የጻፈው ነቢይ(4)

11 በሮማውያን ግዛት ያሉ ሰዎች ሁሉ በሕዝብ ቆጠራ እንዲቆጠሩ የታዘዘው በየትኛው ገዢ ዘመን ነው?(9)

ወደ ታች

7 ኤል እና ኢዮ የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ምን ማለት ነው?(4)

8 እመቤታችንን ከሕጻኑ ጋር በቤተመቅደስ ባገኘው ጊዜ “ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና” ብሎ የተናገረው ሰው(9)

9 ሕይወቱ በሲቃይና በመከራ የተሞላ ስለነበር የመከራ፣ የለቅሶ፣ የሰቆቃ ነቢይ በመባል የሚታወቀው ነቢይ(5)

12 ለጌታችን መባን ሊያቀርቡ በኮበብ ተመርጠው የመጡ የጥበብ ሰዎች(6)

ኦርቶዶክሳዊ ወጣት™